# ሲዳማን ማነው የወከለው?

By Nomona Noto

ስሞኑን ከፌደራል እስከ ወረዳ ደረጃ የምገኙ የሲዳማ ኣመራር ኣባላት በሃዋሳ ከተማ በሲዳማ የወደፊት እጣ ፋንታ ላይ መክረው ባለ ዘጠኝ ነጥብ የኣቋም መግለጫ በማውጣት ኣጠናቀዋል። ኣንዳንዶች እንደምሉት ከሆነ የሲዳማ ኣመራሮች ዳግመኛ በሃዋሳ ከተማ ላለመሰባሰብ የወሰኑ ይመስላል፤ ምክንያቱም የሃዋሳን ከተማ ኣስተዳደር በሌሎች በሳል በምባሉ ብሄሮች እንድተዳደርላቸው ተሰማምተዋል እና ሃዋሳ ከእንግድህ የሲዳማ ኣስተዳደር ኣካል ባለመሆኑ በሃዋሳ ከተማ በሲዳማ ስም የመሰባሰብ እድል የላቸውም ይህንን እንኳን ኣርቆ ማየት ብሳናቸውም።

ወደ ቁምነገሩ ስንመለስ የሲዳማ ህዝብ ኢህኣደግ ይጠቅመኛል በመልካምኣስተዳደር በኩል ያለብኝን ችግር ይፈታልኛል በማለት በተደጋጋሚ በችግሩ ጊዜ ፈጥኖ በመድረስ ሲመርጠው ብቆይም፤ ደኢህዴን/ኢህኣዴግ የሲዳማን ህዝብ ሲያሳዝን የሰሞኑ ክስተት የመጀመሪያው ኣይደለም። የዛሬ ኣስር ኣመት ደምኣፍሳሹ የደኢህዴን መንግስት የጸጥታ ኃይሎቹን ኣሰማርቶ በንጽሃን የሲዳማ ተወላጆችን ላይ በጠራራ ጸሀይ የጥይት መዓት ኣውርዶ በርካታዎቹን በመግደል ሌሎቹን ኣቁስለዋል ፤ በድርግቱም የሲዳማ ህዝብ ክፉኛ ኣዝኗል፤ ሆኖም ከስህተቱ ይማራል ዳግመኛ መሰል ተግባር ኣይደግምም በማለት በባለፈው ምርጫ በነቅስ ወጥቶ እንደመረጠው ይታወሳል። ሰሞኑን ደግሞ ከባለፈው ስህተቱ ያልተማረው ደኢህዴን የሲዳማ ህዝብ ላሳየው ክብር እና ፍቅር የፓርቲው ኣመራሮች የሰጡት ምላሻ ራስን በራስ የማስተዳደር መብቱን በመንጠቅ የራሱን ከተማ በተቀጣሪዎች እንዲያስተዳድር ማድረግ ሆኗል።

የምገርመው ደግሞ የሲዳማ የክልል ጥያቄን የሚያነሱ ኣካላት የሲዳማን ህዝብ የማወክሉ ናቸው ብለዋል። ለሲዳማ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት መከበር ሲሉ በደኢህዴን እስር ቤቶች የሚማቅቁት ብሎም ተሰደው በባዕድ ኣገራት የስደት ኑሮ የምገፉት ውድ የሲዳማ ልጆች ጸረ ሲዳማ ተብለዋል። በተገላብጦሽ ፤የሲዳማ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በመንጠቅ በሃያ ኣመቱ የኢህኣደግ ኣስተዳደር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ህገመንግስታዊ መብቱን በማስነጠቅ የተማረ ሰው የለህም፤ የሃዋሳን ከተማ ማስተዳደር ኣልቻልክም፤ወዘተ በማለት ለዘመናት በህዝቦች ዘንድ ተከብሮ የኖረውን ህዝብ ያዋረዱት የሲዳማ ተወካዮች ናቸው ተብለው ተሞካሽተዋል። እነዚሁ የሲዳማ ህዝብ ተወካዮች ነን ባይ ኣመራሮች የሲዳማ ህዝብ ህልውናማንነት ኣደጋ ላይ ጥለዋል፤ ራስን በራስ የማስተዳደር መብቱን ጥያቄ ውስጥ ከተዋል፤ ሲዳማን ሌሎች እንዲያስተዳድሩት ያለ ህዝቡ ፍላጎት ጋብዘዋል፤ የሲዳማ ህዝብ ራሱን ማስተዳደር ያልቻለ ህዝብ ነው የምል ኣመለካከት ኣብሮት በምኖሩ በሌሎች ብሄሮች እንድፈጠር ኣድርገዋል፤ የሲዳማን ህዝብ የራሱን ግዛት ማስተዳደር ያልቻለ በሃያ ኣንድኣመት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ታሪክ የመጀመሪያው ብሄር እንድሆን ኣድርገውታል፤ ወዘተ።

## እዚህ ላይ ኣንድ የሲዳማ ሃዮ ወይም ምሳሌያዊ ታሪክ ማንሳት እወዳለሁ ። ይሄውም፡- ኣንድ ወቅት የኣንድ የሲዳማ ኣባት መንገድ እየተጓዙ በቃቻ መሃል (በመንደር መካከል) ሲያልፉ ኣንድ ህጻን ምርር ብሎ ስያለቅስ ሰምተው የኣባትነት ኣንጀት ኣላስችል ብሎኣቸው፤ ህጻኑ ወደሚያለቅስበት ግቢ ተጠግተው በኣጥር ተንጠራሪተው ወደሚያለቅሰው ህጻን ሲያዩ ፤ ህጻኑ የምያለቅሰው እናቱ ጸጉሩን እየላጨችው መሆኑን ተረድተው፤ ***ጸጉርህን የምትላጨው እናትህ የያዘህ ደግሞ ኣባት እንግድህ እኔ ምን ላደርግ እችላለሁ*** ብሎ ኣለ ይባላል። እንግድህ ከምሳሌው እንደምንረዳው የሲዳማ ህዝብ እየለጩ ያሉት የራሱ ኣመራሮች ናቸው።

እነዚህ የሲዳማን ኣመራሮች እነማናቸው ብለን ሲናስብ እና የኣንዳንዶቹን የትናንትናውን ስብዕናቸውን ስንገመግም ትንግርት ነው የምሆነው። ትናንትና የምያውቋቸው ዛሬ ላይ ሆነው በሲዳማ ህዝብ የያዙትን ኣቋም ላስተዋለ ሰው በኣስተሳሰባቸው ላይ ያሳዩት ለውጥ እንዴት ልፈጠር እንደቻለ ለማሰብ በራሱ ኣስቸጋር ነው። ለኣብነት ያህል በዩኒቨርስቲ ህይወታቸው ለሲዳማ ህዝብ መብት መከበር የምታገሉ የነበሩት የዛሬዎቹ ኣብዘኛዎቹ የሲዳማ ኣመራሮች፤ ዛሬ ደግሞ በተቃራኒው ቆመዋል። ትናንትና በራሳቸው ያስቡ የነበሩት እነዚሁ ግለሰቦች ዛሬ የሌላ ግለሰብ ኣመለካከት ተቀብሎ ከማራመድ ውጭ ያንን የመሰለ የህዝብ ተቆርቋሪነታቸውን ያንጸባረቁበት ኣመለካከት ውሃ በልቶታል። እንዳው ከደኢህዴን ኣመለካከት ውጭ ማሰብ ኣቅቷቸዋል ማለት እውነታ ኣለው።

እኔ እንደምመስለኝ ከሆነ እንዚህ ኣመራር ኣባላት ባለፉት ጥቂት ኣመታት ማለትም በደኢህዴን መስመር ውስጥ ገብተው መስራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምረው በራሳቸው ማሰብ በማቆማቸው የተባሉትን ከማድረግ ውጭ የራሳቸውን ኣቋም መያዝ ኣቅቷቸዋል።

ለመሆኑ በተለይ በዚህ ሳምንት ያወጡት የኣቋም መግለጫም ሆነ ወሳኔዎቹ በርግጥ የሲዳማን ህዝብ ይጠቅማሉ?ወይስ የሲዳማን ህዝብ ጥቅም ባያስጠብቁም የደኢህዴን ፖሊስ ለማስፈጸም ያህል የተወሰዱ እርምጃዎች ናቸው? ቀጥዬ ማነሳቸው ነጥቦች ናቸው ፤ እመለስበታለሁ።

ለመሆኑ በተለይ በዚህ ሳምንት ያወጡት የኣቋም መግለጫም ሆነ ወሳኔዎቹ በርግጥ የሲዳማን ህዝብ ይጠቅማሉ?ወይስ የሲዳማን ህዝብ ጥቅም ባያስጠብቁም የደኢህዴን ፖሊስ ለማስፈጸም ያህል የተወሰዱ እርምጃዎች ናቸው?

ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ደኢህዴን የዛሬ ሶስት ወራት በፊት የሃዋሳን ከተማ ኣስተዳደር በጋር ለማስተዳደር በምል ያዘጋጀው የውይይት ጽሁፍ ከሰፊው የሲዳማ ህዝብ እጅ ቀድሞ ገብቶ ለእቅዳቸው ኣለመሳካት ለጊዜውም ብሆን ሳንካ ሆኗል። በጊዜው የክልል ባለስልጣናት ስለ የውይይት ጽሁፉ የተለያዩ መግለጫዎችን መስጠታቸው የምታወቅ ሲሆን በደቡብ መገናኛ ብዙሃን ቀርበው *የበሬ ወለደ ወሬ* ነው በማለት ህዝብ ለመዋሸት መሞከራቸው እንዲሁ የምታወስ ነው።

በወቅቱም ብሆን ኣንዳንድ ውስጥ ኣዋቂ ምንጬ እንዳሉት የክልሉ ባለስልጣናት በሬ ወለደ ወሬ ነው በማለት ያስወሩት የሃዋሳ ከተማ ኣስተዳደር የመበረዝ ኣካሄድ ድርጅቱ ጊዜ ወስዶ ተዘጋጅቶበት መክሮ እና ዘክሮ ያዘጋጀው የውይይት ጽሁፍ መሆኑን ነበር። ይህ የሃዋሳን ከተማ ኣስተዳደር ከሲዳማ ተወላጆች ለመንጠቅ ታስቦ የተዘጋጀው ጽሁፍ ሆነ እቅድ በቀላሉ ልሳካ እንደማይችል ኣዘጋጆቹ ጠንቅቀው ስለምያውቁ ነበረ ሃሳቡን ለውይይት ኣዘጋጅተውት የነበሩት። ታዲያ ያን ጊዜ የሲዳማ ህዝብ ባሳየው ህዝባዊ ንቅናቄ ተደናግጠው ሀሳቡን ለማድበስበስ ጥረት ኣድርገው ህዝቡን በማረጋጋቱ ረገድ ተሳክቶላቸው ማለት ይቻላል።

ነገር ግን የወቅቱ የሲዳማ ህዝብ ንቅናቄ ለደኢህዴን ኣመራሮች ኣንድ ትምህርት የሰጣቸው ሲሆን ይህን መሰል በሲዳማ ህዝብ ዘንድ ሰንሴቲቪ የሆነ ጉዳይ እንዲሳካላቸው ካሰፈለገ ጉዳዩን በቀጥታ ከህዝብ ጋር መክሮ ና ዘክሮ ከመወሰን ይልቅ የራሳቸውን ኣመራሮችን ሰብስቦ እንድወሰኑ በማድረግ ካዛም ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወደ ህዝቡ ማውረድ እንደ ብቸኛ ኣማራጭ እንድወስዱ ኣድርጓል። ይህም ታላቅ ስህተት እንዲፈጽሙ ኣድርጓቸዋል። ስለዚህም ኣሁን ጊዚያቸውን ጠብቀው ኣካሄዳቸውን ቀይረው በራሳቸው መወሰን የማይችሉትን የሲዳማ ኣመራሮችን ስብስበው ያለ ህዝቡ ፍቃድና ፈላጎት በሃዋሳ ከተማ ኣስተዳደር ውስጥ ሌሎች ብሄሮችን ለመቀላቀል ወስነዋል። በአቋም መግለጫቸውም የሀዋሳን ከተማ የአመራር ስምሪት ከኪራይ ሰብሳቢነት የጸዳና ብቁ አመራር ከየትኛውም መዋቅር ቢመደብ ትግሉን ለማስቀጠል ቃል ገብተዋል፡፡

ደኢህዴን እንደሞኝ ተረት እየደጋገመ የሃዋሳን ከተማ ከሲዳማ ኣስተዳደር ለመንጠቅ የምዶልተው ጉዳይ የሲዳማ ህዝብ በመንገሸገሹ የተነሳ የሃዋሳ ከተማ ጉዳይ ብሎም ደኢህዴን በሲዳማ ህዝብ ላይ የምፋጽመው ደባ ለኣንደና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንድያገኝ በምል የራሰ የሆነ የክልል ኣስተዳደር ይገባኛል ጥያቄ ኣንግቦ ያደረገውን ከዳር እስከ ዳር ያናወጠ ህዝባዊ ንቅናቄ የሲዳማ ህዝብ ጥያቄ ሳይሆን የጻረ ሰላም ኃይሎች ጥያቄ ነው በማለት ሰፊውን የሲዳማ ህዝብ ጻረ ሰላም ኃይል በማለት የክልሉ ባለስልጣናት ተሳልቀዋል።

የድፍረታቸው ድፍረት እንደፈለጉ በሚያዙት ሚዲያ ቀርበው የሲዳማ የክልል ጥያቄውን ያነሱት ግለሰቦች ናቸው እነርሱም ብሆኑየኪራይ ሰብሳቢ እና የጻረ ሰላም ኃይሎች የህብረተሰቡን አቅጣጫ ለማስቀየር ያደረጉት ጥረት ያለመሳካቱንና ህልማቸው ቢሳካ ኖሮ በውስጠ ድርጅቱ ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ የከፋ ይሆን ነበር ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ ደኢህዴን የምባለው የጥቅት የሲዳማ ኣመራሮች ድርጅት እንጅ ለሲዳማ ህዝብ የቆሞ ድርጅት ኣለመሆኑን የረሱት ይመስላል።

የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ በታየባቸው አንዳንድ አመራሮች ላይም በየደረጃው በተካሄደው የሂስ ግለሂስ መድረኮች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱንም የገለጹት ርዕሰ መስተዳደሩ በቀጣይም የኪራይ ሰብሳቢነትን አስተሳሰብ ከምንጩ የማድረቁ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡እዚህ ላይ ሌላው የረሱት እና ልያውቁት የምገባው ነገር ኣብሯቸው ያሉት ኣመራሮች ቢሆኑ ለሆዳቸው ብለው እንጂ በነጻ ኣዕምሮኣቸው ማሰብ የምችሉ መሆናቸውን ነው። በራሳቸው የምያስቡትንም እና ለሲዳማ ህዝብ ጥቅም መከበር የታገሉ የደኢህዴን ኣመራሮችም ቢሆን በክራይ ስብሳቢነት ልኮነኑ እንደማይገባ ብሎም ዋነኛ ኪራይ ሰብሳቢዎች ጻረ ሲዳማ የሆነት በውሳኔው ላይ የተሳተፉት የሲዳማ ኣመራር ተብዬዎች መሆናቸውን ነው።

በመሆኑም በየጊዜው የሚፈጠሩ የጥገኘነት እና የጻረ ሰላም ኃይሎች የማደነጋገሪያ አጀንዳ የማይበገር አብዮታዊ ስብዕና የተላበሰ የህዝበ መሪነት ሚናችንን እንወጣለን ብለዋል የምሉት ማንን ለማለት እንደፈለጉ ለራሳቸውም ቢሆን ግልጻ የሆነላቸው ኣይመስልም፡፡ምክንያቱም እነዚሁ ኣመራሮች የጻረ ሲዳማ ኃይሎች ጥገኛ ኣመለካከት ኣራማጆች ናቸውና። ከላይ ከኣዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚወርድላቸውን ጻረ ሲዳማ ኣጀንዳ ነው እያስፈጸሙ እንጂ ያሉት ከመቼ ወዲህ ነው በራሳቸው ኣጀንዳ ኖሯቸው ለኣጀንዳቸው መተግበር ሰርተው የምያውቁት?

በኣቋም መግለጫው ላይ ካነሷቸው ጉዳዮች መካከል ሌላው እኔን በተለይ የገረመኝ ጉዳይ የሲዳማ ህዝብ ከሌላቸው ህዝብ ጋር ያለውን ተፋቅሮ የመኖር ባህል በተመለከተ ያነሱት ነጥብ ነው። የሲዳማ ህዝብ ከየትኛውም ብሔር እና ብሔረሰብ ጋር ተፋቅሮ እና ተከባብሮ የኖረ ወደፊትም የሚኖርስለመሆኑ የእነርሱን ምስክርነት ኣያሻውም ነገር ግንለዘመናት ተከባብሮና ተዋዶ የኖረውን የሲዳማንና የወላይታን ህዝብ ለማጋጨት ብሎም ለማለያየት ሲንቀሳቀሱ…በማለት በኣቋም መግለጫቸው ያነሷት ነጥብ ወዴት ወዴት እንድል ኣስብሎኛል። ምክንያቱም በሲዳማ እና ወላይታ ህዝቦች መካከል የተለየ ግጭት የለም ኖሮም ኣያውቅም፤ ባይሆን ሆኖም ግጭት እንዳለ ኣስመስለው መግለጨ ስጥተዋል።

ከላይ እንዳነሳሁት የሰሞኑ ውሳኔው የሲዳማን ህዝብ ልጠቅም የምችልበት ሁኔታ ምን እንደሆነ በግልጽ እነኝሁ የሲዳማ ኣመራሮች መግለጽ ኣልቻሉም። እንዳውም ከግል ጥቅም ኣንጻር ካልሆነ በስተቀር የሃዋሳን ከተማ ኣስተዳደር የሲዳማ ህዝብ በመንጠቅ ለሌላው መስጠት እንዴት ሲዳማን ልጠቅም እንደምችል ለማብራራት እነሱም ብሆኑ ትንሽም ብሆን ረቀቅ ያለ ኣእምሮ ሳያስፈልጋቸው ኣይቀርም፤ በኣጠቃላይ የፍቅር ከተማዋን መነጠቅ ለሲዳማ እንዴት ነው የምጠቅመው?የራሱን ለሌላው ኣሳልፎ እየሰጠ እንዴት ነው ተጠቃሚ የምሆነው?

እንደምናውቀው የሲዳማ ህዝብ ጥያቄ እና ፍላጎት የኣስተዳዳር ኣከባቢውን በክልል ደረጃ ማስተዳደር ነው። የሲዳማ ህዝብ ለዚሁ ዓላማ ላለፉት ከሰላሳ በላይ ዓመታት ልጆቹን መስዋዕት ኣድርጓል በማድረግም ላይ ነው። ታዲያ የህዝቡ ፍላጎት የሃዋሳን ከተማ ኣስተዳደር መነጠቅ ሳይሆን ከዛም ባለፈ የራሱን ክልላዊ ኣስተዳደር መመስረት ነው። የህዝቡ ፈላጎት ይህ በሆነበት በኣሁኑ ወቅት ይህ መሰል የህዝቡን ፈላጎት ያላገናዘበ ውሳኔ መውሰድ የሲዳማ ህዝብ ፋላጎት እና ጥቅም ከማስጠበው ይልቅ የደኢህዴንን ፈላጎት ማስጠበቅ ነው።

ደኢህዴን የሲዳማን ህዝብ ፍላጎት እና ጥቅም ካላስጠበቀ ለሲዳማ ህዝብ ምኑ ነው? እኔ እንደማስበው ከሆነ በየትኛው ዓለም የምገኙት መንግስታት እና የፖለቲካ ድርጅቶች የቆሙላቸውን ህዝብ ፈላጎት እና ጥቅም ለማስጠበቅ ቀን ለሌት ስሰሩ ነው የምታዩ እንጂ በየትኛውም ኣጋጣም ከወከለው ህዝብ በተቃራኒ የቆሞ ድርጅት በታሪክ የለም ከደኢህዴን በስተቀር ማለት ነው።ደኢህዴን ከውሳኔ በኃላ ህዝቡን በውሳኔያቸው ላይ ለማወያየት ዳርዳር እያለ ነው። ተሳክቶላቸው እንኳን ህዝቡን ማሰባሰብ ከቻሉ፤ እኔ ኣሁን እያጓጓኝ ያለው የሲዳማ ኣመራሮች ያሳለፉት ውሳኔ የሲዳማን ህዝብ እንዴት ልጠቅም እንደምችል ለህዝቡ ቀርበው የምያብራሩበት ጊዜ ነው።